2

አፍሪካ ቲቪ

# አፍሪካ አካዳሚ

AFRICA ACADEMY

www.AfricaAcademy.com

# ሁሉም ሙስሊም ማወቅ ያለበት አዝካር ፣ ዱዓዕ እና ከፍተኛ ምንዳ ያላቸው ሥራዎች 5

በቴሌግራም

AAcademyEthio

www.AfricaAcademy.com

- **ከሲህር (ድግምትና) ከዐይን ስለ መጠንቀቅ፤**

- መተትና ድግምትም ሆነ አይነ-ናስ ከመከሰቱ በፊት ራሳችንን ከእሱ እንዴት እንደምንጠብቅ ማወቅ ያስፈልገናል፡፡ በቅድሚያ መጠንቀቅ ከተያዙ በኋላ በህክምና ከመማቀቅ ይሻላልና፡፡

✓ **መጠንቀቅ በብዙ ነገሮች ይቻላል፡፡** ከእነነፍስን በተውሂድ ማጠናከር- ይህችን ዐለም እንደ ፈለገ የሚያስተናብር አላህ (عز وجل) ብቻ መሆኑን ማወቅና መልካም ተግባሮችን ማብዛት፤

✓ **ከአላህ (ﷻ) ደግን ማሰብና መጠርጠር፣** በእሱ ብቻ መመካት፤ በሽታውን ከየት መጣ፤ በምን መጣብኝ ብሎ አለማሰብ አለመጨነቅ፡፡ ምክንያቱም ሐሳብ እራሱ በሽታ ነውና፡፡

- **ዚህም መካከል ዋናው፡-**

✓አይኑ ጉዳት ያደርሳል (በተለምዶ ቡዳ ነው) ተብሎ የታወቀን ሰው ፈርቶ ሳይሆን ለጥንቃቄ ሲባል መሸሽ ያስፈልጋል፤

✓ደስ የሚል ነገር ስታይ ባረከሏህ (ማሻአላህ) በማለት አላህን (ﷻ) ማውሳት ይገባል፡፡

ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ሐኪም በዘገቡት ሐዲስ (ከራሱም ሆነ ከገንዘቡ ወይም ከወንድሙ የሚያስደስተው ነገርን ያየ ሰው ባረከሏሁ ይበል ምክኒያቱም አይነ-ናስ (ዐይን) ሐቅ ነውና፡፡) ብለዋል፡፡

✓ጧት ጧት በባዶ ሆድ ከዐጀዋ (የመዲና ቴምር) ሰባት ፍሬ መብላት፤



AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com

✓ወደ አላህ መጠጋትና በሱ ላይ መመካት፤ የጧትና የማታን ዚክር ማዘውተር፤ ከሁሉ ነገር በአላህ መጠበቅ፤ ዚክሮች ብዙ ውጤቶች አሏቸው፡፡

በአላህ (ﷻ) ፍቃድም ዚክሮች በአላህ ፈቃድ በሁለት ነገሮች ምክንያት ሊቀንስና ሊጨምር የሚችል ተፅዕኖ አላቸው፡፡

1) በውስጡ ያለው ነገር ሁሉ ሐቅ ነው፡፡ በአላህ (ﷻ) ፍቃድም ይጠቅማል ብሎ ማመን፤

2) ምላሱ ሲናገረው ጆሮው አዳምጦ፤ በልቡ ህያው ሆኖ ዱዓ መሆኑን ሳይዘናጋ ካደረገው ነው፡፡

- **የዚክርና የተዐውዝ (ከአላህ (ﷻ) ጥበቃን የምንጠይቅበት) ጠብቀን የምንልበት ጊዜ (ሰዓቶች):-**
  የጧት ዚክሮች የሚባሉት ከሱብሂ ሶላት በኋላ ነው። የማታ ዚክሮች ደግሞ ከአስር ሶላት በኋላ ነው የሚባሉት። ከረሳው ወይም ከተሳነፈ ሲያስታውሰው ይላል።

- **በአይነ-ናስ (በሰው ዐይንም) ሆነ በሌላ የመያዝ ምልክቶች ፤**

በዘመናዊ ህክምናና በሸሪዓዊ ሩቅያ (በኢስላም መንፈሣዊ ህክምና) መካከል ግጭት ብዙም የለም።

- ቁርኣን ለአካላዊም ሆነ ለመንፈሳዊ በሽታዎች ሁሉ ፍቱን ፈውስ ነው።

- ሰውየው ከአካላዊ በሽታዎች ነፃ ከሆነ የዓይንናስ መሰል በሽታ ምልክቶቹ :- የሚፈራረቅ የራስ ህመም፤ የፊት መገርጣት፤ የላብና ሽንት መብዛት፤ የፍላጎት መቀነስ፤ በሰውነት ጫፎች ላይ ተነሙል (የመደንዘዝ ባህሪ)፤ ቁስል መብዛት፤ ወይም ሙቀት ወይም ቅዝቃዜ መታየት፤ የልብ ማንቋረት፤ ከወገብ በታችና በትከሻ ላይ በሁለቱ መካከል የሚመላለስ የህመም ስሜት፤ ሀሳብ፤ ሀዘንና ጭንቀት በልብ ላይ መብዛት፤ የሌሊት እንቅልፍ ማጣት፤ ያልተለመደ የቁጣ የፍርሃትና የመገንፈል ስሜት መብዛት፤ ከልክ ያለፈ ማግሳት፤ ብቸኝነትን መውደድ፤ መስነፍና መሰላቸት (መዝለፍለፍ)፤ እንቅልፍ እንቅልፍ የማለት ስሜት፤ ሌሎች በህክምና ምክንያታቸው ያልታወቁ የጤና መታወክ ማጋጠም ናቸው፡፡
- በበሽታው የጥንካሬና ድክመት ልክ ከተጠቀሱት ምልክቶች ሁሉም ወይም አንዳንዶቹ በበሽተኛው ላይ ሊከሰቱ ይችላሉ፡፡

- አንድ ሙስሊም ሁልጊዜም ማንኛውም ወስዋስ የማያጠቃው ጠንካራ እምነትና ቀልብ ሊኖረው ይገባል፡፡

- ከእነኚህ ምልክቶች አንዱን በማየቱ ብቻ በሆነ በሽታ ተለክፌያለሁ ብሎ ሊጨነቅ አይገባም፡፡ ጭንቀት ራሱ ለህክምና አስቸጋሪ የሆነ በሽታ ነውና፡፡

- በአንዳንድ ጤነኛ ሰዎች ላይም እነኚህ ምልክቶች ሊታዩ ይችላሉ፡፡ በሽታው አካላዊም ሆኖ እነዚህ ምልክቶች ሊታዩ ይችላል፡፡ የሀሣብና የጭንቀት መብዛት ምክኒያቱ የኢማን (እምነት) ድክመት ሊሆን ይችላል፡፡ ስለዚህ አንድ አማኝ ሁሌም ከአላህ (ﷻ) ጋር ያለውን ግንኙነት መገምገምና ራሱን ማጠናከር ይገባዋል፡፡

- ህመሙ በአይነናስ ምክኒያት ከሆነ ፈውሱ (ህክምናው) በአላህ ፈቃድ ከሁለት በአንዱ ይሆናል፡፡
- 1) ባለ አይኑን ሰው ካወቅከው እንዲታጠብልህ (ውዱዕ እንዲያደርግ) ጠይቀህ ወይም ከሱ የነካካውን ቅሪት (ዱካ) አንዱን ወስደህ በዚያ ውሃ መታጠብና መጠጣት ነው፡፡
- 2) አይናማው ሰው ካልታወቀ በሸሪዓዊ ሩቅያ፣
  በዱዓና በዋግምት ነው፡፡



www.AfricaAcademy.com
AAcademyEthio

- ህመሙ በመተት (ድግምት) አስማት ምክንያት የተከሰተ ከሆነ ደግሞ ፈውሱ በአላህ ፈቃድ ከዚህ በታች ከተጠቀሱት በአንዱ ይሆናል፡፡

- **1)** አስማቱ ያለበትን ቦታ ካወቀው ሁለቱን ቁል አዑዙዎች (ቁል-አዑዙ ቢረቢናስን እና ቁል-አዑዙ ቢረቢልፈለቅን) እያነበበ መተቱን (ድግምቱን) አውጥቶ በእሳት ማቃጠል፤

- **2)** በሸሪዓዊ የፈውስ አደራረግ፤ ይህም ከቁርአን አንቀጾች በተለይም ቁል አዑዙዎች በበቀራህ ምዕራፍና ከዚህ ቀጥለው በሚመጡት ዱዓዎች እያነበቡ
ሩቅያ ማድረግ ነው፡፡

- **3)** 'ኑሽራ' ድግምቱን ማስፈታት ሲሆን፡- ይኸውም በሁለት አይነት ይከፈላል፡፡

አፍሪካ አካዳሚ

1) ክልክል የሆነው ሲሆን - ይኸውም ድግምትን በድግምት መፍታትና ለዚሁ ጉዳይ ወደ ድግምተኞች መሄድ ነው፡፡

2) የሚፈቀድ አይነት ሲሆን- ይህም (ሰባት የቁርቁራ ቅጠል በድንጋይ ፈጭቶ ከዚያም ሶስት ጊዜ ሱረቱል-ካፊሩን፤ ሱረቱል-ኢኽላስንና ሁለቱን ቁል አዑዙዎች አንብቦ በውሃ በጥብጦ መጠጣትና መታጠብ እስከሚድን ድረስ ይህን ደጋግሞ ማድረግ ነው፡፡ ኢንሻአላህ በአላህ ፈቃድ ፈውስ ይገኝበታል፡፡) ዐብዱረዛቅ የዘገቡት ሐዲስ ነው፡፡

- **4)** ድግምቱ በሆድ ውስጥ ከሆነ ወደታች በሚያስቀምጥ ነገር ማስወጣት ይቻላል፡፡

- ከሌላ ላይ ከሆነ ግን በዋግምት ማስወጣት ነው፡፡

2